# <u>የዓለም ባንክና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ሚና</u>

ከ

ዶ/ር ሠይድ ሀሰን

## <u>ሀ) መግቢያ</u>

የዓለም ባንክና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (World Bank and International Monetary Fund (IMF)) በተለይ ከ1997ቱ ህዝባዊ ምርጫ በሁዋላ አቋማቸዉን መለወጣቸውና ከጨቋኙ ከሕወሓት አገዛዝ ጋር መተባበራቸው ብዙ ኢትዮጵያውያንን ማበሳጨቱ እሙን ነው። ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት አንዳንድ ድህረ-ገጾችና የሬድዮ ጣቢያዎች ምሁራንን በመጋበዝ አወያይተዋል። ማብራሪያዎችም አቅርበዋል።
ይህ ጽሁፍ በድህረ-ገጾቹና በሬድዮ ጣቢያዎቹ የቀረቡትን ላልሰሙና ተጨማሪም ማብራሪያ ለሚፈልጉ ታስቦ ባጭሩ የቀረበ ነው። በቅድሚያ ግን የገንዘብ ድርጅቶቹ እንዴትና ለምን እንደተቋቋሙ ለመረዳት ይረዳ ዘንድ አንዳንድ መነሻ ሃሳቦችን ለመንደርደርያ እናቅርብላችሁ።

## 1) <u>የዓለም ባንክ አመሰራረትና ቀዳሚ ዓላማ</u>

የዓለም ባንክ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1944/1945 ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንደተገባደደ ነበር የተቋቋመው። የተቋቋመበት ቀዳሚ ምክንያትም በጦርነት የደቀቁትን በተለይም የምዕራብ አውሮፓ አገሮችን ኤኮኖሚ ለመጠገን ታስቦ ሲሆን በወቅቱ ገንዘብ ከነበራቸው አገሮች፣ ሀብታሞችና ኩባንያዎች ገንዘብ ሰብስቦ ይህንኑ የተሰበሰበ ገንዘብ በጦርነቱ የተጎዱት አገሮች እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ነበር። እነዚህ አገሮች ራሳቸዉን ከቻሉ በኋላ ግን የዚህ ድርጅት ዋና ተግባር ተቀይሮ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ድሃ አገሮች ብቻ ብድር እንዲሠጥ ተወሠነ፤ ሚናውም ተለወጠ። ገንዘብ ከማበደር በተጨማሪም "አዋቂዎችን" ለታዳጊ አገሮች ማቅረብን እንደተጨማሪ ዋነኛ ተግባሩ አደረገ። ባንዳንድ ምሁራን ጥናት ውስጥ እንደቀረበው ግን ወደ ድሃ ሃገሮች የሚላኩ "አዋቂዎች" የሚከፈላቸው ገንዘብም ሆነ የሚሰጣቸው ስልጣን ከተገቢው በላይ ስለሆነ በብድር ለድሃ ሃገሮች የሚሰጠውን ገንዘብ ከፊሉን ወደመጡበት አገር ይዘው እንዲመለሱ ያስቻለ፤ የአንዳንዶቹም የሕይወት ታሪክ ሲመረመር በየሃገሮቻቸው ሥራ አጥ የነበሩ በመሆናቸው ባንኩ ሥራ የከፈተላቸው፤ ሌሎቹም ወደ ድሆቹ ተበዳሪ አገሮች ሲላኩ ቀደም ብለው ለማያውቁት የኢኮኖሚ አመሠራረት፣ ባህልና ልምድ አጋልጦ እንኩዋንስ ስለኤኮኖሚ ጉዳይ በበቂ ሊያማክሩ ቀርቶ ከአገሮቹ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማይጣጣሙና የተሳሳቱ ምክሮችንና መመሪያዎችን እየሰጡ በአገሮቹ ላይ ጉዳቶችን ማድረሳቸው ጭምር ተረጋግጧል። ባገራችን ምሣሌያዊ አነጋገር "አላዋቂ ሣሚ ንፍጥ ይለቀልቃል" እንደሚባለው መሆኑ ነው!

## 2) <u>የዓለም የገንዘብ ድርጅት አመሰራረትና ቀዳሚ ዓላማ</u>

እንደዓለም ባንክ ሁሉ የዓለም የገንዘብ ድርጅትም የተቋቋመው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1944/1945 ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መገባደድ በኋላ ነው። የተቋቋመባቸው ዋነኛ ዓላማዎችም፦

1. አንዳንድ አገሮች ከሌሎች አገሮች ጋር የንግድ ልውውጥ በሚያደርጉበት ወቅት ገንዘብ ሲያንሳቸው ለማበደርና ዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጡ እንዲቀላጠፍ ለማስቻል፤

2. የአንድን አገር ገንዘብ በሌላ አገር ገንዘብ ያለብዙ ችግር በቀላሉ መቀየርና ቅያሪውንም መተመን እንዲቻል ለማድረግ፤ አግረመንገድንም ምቹ የገንዘብ ልውውጥ ሁኔታን ለመፍጠር፤
3. ድርጅቱ በተመሰረተበት ወቅትና ከዚያም በፊት አንዳንድ አገሮች የራሳቸዉን ገንዘብ የልውውጥ ተመን ሆን ብለው ዝቅ በማድረግና የአገራቸውን ዕቃዎች (ፍጆታዎች) ዋጋ ዝቅ በማድረግ በሌሎች አገሮች ላይ ተጽዕኖ እንዳያደርጉ፤ ይህንን ዓይነት ዘዴም በመከተል አገሮች የራስን አገር ጥቅም ብቻ አስጠባቂ እርምጃ እንዳይከተሉና የገንዘባቸውን ዋጋ እጅጉን ዝቅ በማድረግ ላይ የተመረኮዘ የመጠፋፋት የንግድ ፉክክር እንዳያስፋፉ ለማገድና ለመቆጣጠር (to stop competitive devaluation)፤
4. አንዳንድ አገሮች ያለውዴታቸው የገንዘባቸው ዋጋ ሲያሽቆለቁልባቸው ወይም ሲንኮታኮትባቸው የውጭ ምንዛሪን እንደድጋፍ በብድር በማቅረብ ድጋፍ ለመስጠት፤
5. እንደዓለም ባንክ ሁሉ "አዋቂዎችን" በማቅረብ ድሃ ሃገሮችን ለመርዳት ናቸው።

ይሁን እንጂ ዛሬ የዓለም የገንዘብ ድርጅት ከሚከሰሰባቸው ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ ቀስ በቀስ የዓለም ባንክ መሥራት የሚገባው የብድር ሥራ ላይ በሰፊው መሰማራቱና የባንኩን ጥቅም መጋፋቱ ነው። ሁለቱን ድርጅቶች ተመሣሣይ የሚያደርጓቸው ጉዳዮች ደግሞ ሁለቱም ገንዘብ አበዳሪ ድርጅቶች በመሆናቸው ያለ ተበዳሪ ሊኖሩ የማይችሉ፤ አዋቂዎችን አቅራቢ ነን ባዮች መሆናቸውና) በብድር ድጋፍ ስም በተበዳሪ አገሮች ላይ ጫናና ግፊት ማድረጋቸው ናቸው።

ለ) <u>የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት አወዛጋቢ ባሕርያት</u>

የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት ዛሬ አወዛጋቢ ከመሆንም አልፈው በብዙ አገሮች መንግስታትና ህዝቦች በበጎ የሚታዩ አይደሉም። አወዛጋቢ የመሆናቸው ዋነኛ ምክንያቶችም በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ውስጥ በተግባር ባሳይውዋቸው የአሰራር ባሕርያቶቻቸው ናቸው።
<u>በሶስተኛ ዓለም አገሮች ወይም በታዳጊ አገሮች ውስጥ የታዩ የአሰራር ባሕርያት፦</u> አብዛኛውን ጊዜ የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት ለታዳጊ ወይም ለሶስተኛ ዓለም ሃገሮች ገንዘብ ሲያበድሩ ሃገሮቹ እንዲያሟሉ የሚጠይቋቸው ሁኔታዎች (conditionalities) ይበዛሉ። ከፍተኛ ጫናም ያደርጋሉ። የተጠቀሱትን ሃገሮች የገንዘባችሁን የምንዛሬ ዋጋ ዝቅ አድርጉ (devaluate) ብለው ከመገፋፋታቸውም በላይ በተዘዋዋሪም ያስገድዳሉ። የድሆች ወይም የታዳጊ አገሮች መንግስታት ለህዝባቸው የሚያደርጉትን ለምሳሌ እንደጡረታ ዓይነት ክፍያዎችም እንዲቀንሱ ያስገደዱባቸው ቦታዎች አሉ። ሃገሮቹም የተባሉትን በማድረጋቸው ነዋሪው ሕዝብ የበለጠ የሚጎዳበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በሌላም በኩል የመንግስት ሀብት የሆኑ ኩባንያዎችንና ድርጅቶችን ወደ ግለሰብ ሃብት መዘዋወር አለባቸው በማለት ተጽዕኖ ማድረሳቸው ተዘግቧል። ብዙ ጥናትና ጥንቃቄ ሳይደረግና ህዝቡም ሳይመክርበት በመንግስት የተያዙ ኩባንያዎችና የኢኮኖሚ አውታሮች ወደ ግለሰቦች እጅ በርካሽ እንዲገቡ በማድረጋቸውና እንደነዚህ ዓይነት ግፊቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ ሲያደርጉም የተጎዳው የህብረተሰብ ክፍል አቅመቢሱና ድሀው ነው። በዚህም ምክንያት ድሃው ህዝብ እየተቆጣ አንዳንድ ጊዜ በመንግስት ላይ ያምጻል። አመጹ ሲባባስም ባገሪቱ ወስጥ ሁከት ይፈጠራል። ይህንኑ ተከትሎም የሰው ህይወትና ንብረት መጥፋት ይመጣል፤ ጠፍቷልም። ይህም በበኩሉ የድሃ አገሮችን ችግር አባብሷል። እንደነዚህ አይነት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ደግሞ፦
1) አንዳንድ አገራቸዉንና ህዝባቸዉን የሚወዱ መሪዎች ከአበዳሪዎቹ የሚመጣውን ጫና መቃወማቸው አልቀረም፤ የሚገፋዉንም ትዕዛዝ አንቀበልም ማለት ግዴታ ሆኗል። ይህን ካደረጉ አገሮች በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉት ማሌዥያ፣ ደቡብ ኮሪያና በመጠኑም ቢሆን ሩሲያ ናቸው።
2) አንዳንድ መሪዎች ደግሞ የደረሰዉን ችግር በነዚህ ድርጅቶች በተለይም በዓለም የገንዘብ

ድርጅት ላይ በማላከክ ችግሩን ያመጡት እነዚሁ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መሆናቸውን ለህዝባቸው በድፍረት መግለፃቸው አልቀረም። መሪዎቹ እግረመንገዳቸውን የአዞ እንባም አንብተዋል።

3) በአኳያው አንዳንድ ጨቋኝና አምባገነን መሪዎች ከነዚህ ድርጅቶች የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ መቀበልን መርጠዋል። እንደነዚህ ያሉ መሪዎች ከነዚህ ድርጅቶች የሚሰጠውን የብድር ገንዘብ እንደ ትልቅ አስተዋፅኦ በመቁጠር ብድሩ እነሱ በሥልጣን ላይ ባይሆኑ ኖሮ ጨርሶ እንደማይገኝ አድርገው በኩራት ለህዝባቸው በመገናኛ መሣሪያዎች ጭምር አሥራጭተዋል፤ አገራቸውንም ሕዝባቸውንም የዘላለም ባለዕዳና ተበዳሪ አድርገዋል። ይህ በተለይ በኢትዮጵያ የተከሰተ ሃቅ ነው።

አገራቸውንም ሕዝባቸውንም ባለዕዳና ተበዳሪ የሚያደርጉ የኒህን ዓይነቶቹ መሪዎች ጠባዮች ደግሞ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው። እኒህን ዓይነቶቹ መሪዎች አብዛኞቹ፦

ሀ) ደካማና የህዝብ ድጋፍ የሌላቸው በአገሩ ደግሞ በውጭ ድጋፍ የሚመኩ፤ የሚደጎሙ፤ ወይም

ለ) ጨቋኞችና አምባገነኖች፤ ወይም

ሐ) ከአበዳሪ ወዳጆቻቸው ጋር ሆነው ህዝቡን ከሚበዘብዙት አጋሮቻቸው ጥቅም በስተቀር ለሚገዙት ህዝብ ደንታ የሌላቸው፤ ወይም

ሠ) በዕርዳታው ሰበብ የሚሰጣቸውን የውጭ ምንዛሪ ወደ አገራቸው ካስገቡ በኋላ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ዕዳ የሆነን ገንዘብ በመስረቅ ያላግባብ ሃብት አካብተው የሰርቀሹን ሃብት በተዘዋዋሪ ወደ ውጭ አገር ባንኮች በራሣቸው ሥም በማዘዋወር ለራሳቸው ጥቅም ያጋበሱ ናቸው። ለዚህ በአብነት የቀድሞዎቹን የፊሊፒንስ መሪ ፈርድናንድ ማርቆስ፤ የዛየሩ ሞቡቱ ሴሴኮ እንዲሁም አሁን በስልጣን ላይ ያሉ በርከት ያሉ የአፍሪካ አገሮች መሪዎችን መጥቀስ ይቻላል። ከላይ የጠቀስነው ይህን መሰል ክስተት በቀዳሚነት የሚጠቀስና ዓለማቀፎቹ የገንዘብ ድርጅቶች በበጉ እንዳይታዩ ካደረጓቸው ምክንያቶች ዋነኛው ነው።

ሌላው ዓቢይ ምክንያት ደግሞ ከአበዳሪዎቹ የስራ ባሕርይ ጋር እጅጉን የተያያዘና ከዚሁም የሚመነጭ ችግር ነው። የዓለም ባንክና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በእርግጥም ገንዘብ አበዳሪ ድርጅቶች ናቸው። ተበዳሪ አገሮችም የተለያዩ ችግሮች የሚበዙባቸው በጣም ድሆች ናቸው። ስለሆነም፤

1. እንደማንኛውም አበዳሪ እነዚህ ዓለማቀፋዊ የገንዘብ ድርጅቶች ሁልጊዜም ገንዘብ ለማበደር አቆብቁበው ይጠብቃሉ።

2. በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችም የሥራ ዋስትናቸው ብድር ስለሆነ ወጥተውም ወርደውም፤ ጨልሞም ነግቶም፤ ብድር ማበደር አለባቸው። ብድሩ ለተበዳሪዎች ይጥቀም አይጥቀም የነሱ ችግር አይደለም። አንዳንድ ጊዜም ብድሩ ተግባራዊ ሲሆን አንዳንዶቹ የጉቦ ክፍያ ያገኛሉ። ለምሣሌ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1998 በአሜሪካ ቴሌቪዥንና ጋዜጦች ላይ አንዳንድ የአፍሪካ አገሮች ብድር ለማግኘት ሲሉ በወቅቱ በድርጅቶቹ ውስጥ ይሰሩ ለነበሩ ሠራተኞች ጉቦ እንዳቀበሉ አስታውቀዋል። ከነዚህም አገሮች መካከል የአፍሪካ ቀንድ አገሮች ይገኙበት እንደነበሩ ገልፀዋል።

3. በሌላ በኩል ዓለማቀፎቹ የገንዘብ ድርጅቶች ብድር ሲፈቅዱ ዕቃቸው የሚሸጥላቸው ኩባንያዎችና አገሮች ብድሩ እንዲሣካ ይጥሩ ወይም ይገፉ እንደነበርም ታውቋል። ይህም በመሆኑ፦

4. ተበዳሪ ሃገሮች ከተወሰኑ አገሮች እቃዎች እንዲገዙና የነዚህ አገሮች ባንኮች ብድሩን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሚና እንዲኖራቸው ሁኔታው አስገድዷል። ለምሣሌ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1990ቹ መጨረሻ ላይ ኢትዮጵያ ቦይንግ ከተባለው የአሜሪካ ኩባንያ ሁለት አውሮፕላኖችን ስትገዛ የአሜሪካ ባንኮች ኢትዮጵያ ብድሩን ከእኛ መውሠድ አለባት በማለት አራጣውንም በጣም ከፍ በማድረግና የኢትዮጵያን አየር መንገድ በሚጎዳ ሁኔታ የተደረገውን አሳዛኝ ተግባር ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ከላይ የጠቀስናቸው ሁኔታዎች የሚያብራሩት፦

- ብድር ለተበዳሪ አገር ጠቀመም አልጠቀመም ብድሩ እንዲሣካ የሚገፉፉ ሌሎች ተጠቃሚ ሀይሎች፤ አገሮች፤ ድርጅቶችና ግለሰቦች መኖራቸውን፤
- ለተበዳሪ ሃገሮች የአበዳሪ ድርጅቶች መኖር መጠነኛ ድጋፍን ቢሰጥም በመሰረቱ ግን ተበዳሪዎችን "ብናጠፋ እነዚህ ድርጅቶች ይረዱናል" የሚል የተሳሳተ ግንዛቤን ስለሚያሳድር በእጅ አዙርም ግዴለሽነትን ስለሚያስከትል ብሎም ሙስናን (corruption) ስለሚያበረታታ ከጥቅሙ ጉዳቱ ማመዘኑ አልቀረም። "አበዳሪዎቻችን እስካሉ ድረስ አንቸገርም" የሚለው አማላይ አስተሣሠብ ዞሮ ዞሮ የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት እንደዋስትና (insurance policy) እየተቆጠሩ የተበዳሪ ሃገሮችን ባለስልጣናት በሥልጣን እንዲባልጉ ይጋብዛል።
- እንዳውም አንዳንድ ምሁራን እነዚህ የገንዘብ ድርጅቶች ለተበዳሪ ሃገሮች ከሚሰጡት ጥቅም ይልቅ አገልጋይነታቸው ለሀብታም አገሮችና አበዳሪ ባንኮቻቸው ብድር ስብሳቢ ማድረግ በመሆኑ የድርጅቶቹ ሚና እጅጉን አወዛጋቢ ነው ሲሉ በግልጽ በጥናት ፅሁፎቻቸው ላይ ለመግለፅ አስደፍሯቸዋል።

## ሐ) <u>የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት ያደረጉት አስተዋፅኦና ያደረሱት በደል</u>

በቀዳሚው የዚህ ፅሁፍ ክፍል የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅትን አወዛጋቢ ሚና ተመልክተናል። እዚህ ላይ ለመሆኑ እኒህ ድርጅቶች በሚሰጡት ብድር ተጠቅመው ከችግራቸው የተላቀቁ አገሮች የሉምን? ካሉ ስንትና እነማን ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀርም። ጥያቄያችንን ጠለቅና ሰፋ እናድርገው ካልንም ለመሆኑ እነዚህ ድርጅቶች በገንዘብ ነክ ጉዳይ እውን አዋቂዎች ከሆኑ እንደምን ድሃ ሃገሮች ችግር ላይ ከመውደቃችው በፊትና የገንዘቦቻቸው ዋጋ ከመንኮታኮቱ በፊት አይደርሱላቸውም? በነዚሁ ሃገሮች ውስጥ የከፋ ችግር ከመድረሱ አስቀድሞስ ለምን ችግሮቻቸውን ለመጋራት ጥረት ማድረግ አልቻሉም? እንዴትስ ይህን ማድረግ ተሳናቸው? የሚሉ ጥያቄዎችም አከታትሎ ማንሳት ይቻላል። በአጠቃላይ ለመሆኑ የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት ለ60 ዓመታት ያህል በገንዘብ ነክ ሥራ ላይ ሲቆዩ ያስገኟቸው ድሎች አሉን? የሚለው ጥያቄ በቂ መልስ የሚሻ ነው። አንዳንድ ምሁራንና አዋቂዎች ግን እኒህ የገንዘብ ድርጅቶች ካስገኟቸው ድሎች ይልቅ ስለቀፈቀፏቸው ችግሮች በሰፊው ማተትን በመምረጥ ተቃውሟቸውን ከፍ አድርገው ሲያሰሙ ነው የሚደመጡ።

የተቃውሟቸውን ምክንያቶች ሲያብራሩም፦

1. ብድሩ ከድህነት የሚያላቅቅ ቢሆን ኖሮ ተበዳሪ አገሮች ሁልጊዜም ደጋግመው ተበዳሪና ለማኝ ባልሆኑ ነበር። እንዳውም ባለፉት 30 እና 40 አመታት ውስጥ ከነዚህ ድርጅቶች ተበዳሪ የነበሩ አገሮች አብዛኛዎቹ አሁንም ተበዳሪዎችና ድሆች፤ እንዳውም ብድሩ በዝቶባቸው የዕዳ ቅነሳ ልመና የሚያሰሙ ናቸው።

2. የተበዳሪ አገሮች ኢኮኖሚ እጅግ ከመድቀቁ የተነሳ በሃብታምና በድሀ አገሮች ያለው ልዩነት በጣሙን ሰፍቷል፤ ድሃው ወደ ድህነቱ ሲያሽቆለቁል ሀብታም አገሮች በሀብት በልፅገዋል። እንዳውም ተበዳሪዎች ብድሩ በየጊዜው እየጨመረ ይበልጥ ባለዕዳ አድርጓቸዋል።
3. "የአበዳሪ ድርጅቶችን ምክር አንቀበልም፤ የተበደርነውን ገንዘብ በሚመለከት ከችግራችን ስንወጣና መክፈል ስንችል ቀስ በቀስ እንከፍላችኋለን፤ አገራችን ውስጥ የሚገኘው ሀብታችሁ

ባስቸኳይ ካገራችን ሊወጣ አይችልም፤ ቁጥጥር እናደርጋለን" ያሉ እንደቺሊ (በ1970ቹ አጋማሽ) ደቡብ ኮርያ ማሌዥያና ሩሲያ (በ1990ዎቹ ዓመታት) ያደረጓቸው የእምቢታ እርምጃዎች ደግሞ ለሌሎች ጠቃሚ ምክሮችን የሰጡ ቢሆንም ከነዚሁ ውስጥ አሁንም ከችግሮቻቸው ጨርሶ ያልተላቀቁ መኖራቸው የራሱ አንዳች ልምድ ሰጥቶ አልፏል። የተጠቀሱት አገሮች ቀስ በቀስ ከችግሮቻቸው ሲላቀቁ የገንዘብ ድርጅቶቹን ምክር አሜን ብለው ከተቀበሉትና ተመሣሣይ ችግሮች ካጋጠሟቸው ሌሎች አገሮች ጋር ሲወዳደሩ ከችግሮቻቸው ለመዉጣት ጥቂት ግዜ የፈጀባቸው ሲሆን ምክሩን ከተቀበሉት አገሮች ውስጥም አንዳንዶቹ አሁንም በችግር ላይ ናቸው። አሻፈረኝ ባሉት አገሮች ላይ የገንዘብ ድርጅቶቹ ያደረሱት ቁጣም ምንም ጉዳት እንዳላሳደረባቸው ለማወቅ በመቻሉ አበዳሪዎችን እንደዋስትና መቁጠሩ ፋይዳ እንደሌለው በግልፅ አሳይቷል።

4. በተለይ አንዳንድ ፀሃፊዎች ካቀረቧቸው ግልፅ ተቃውሞዎች መካከል፦

- በቀዳሚነት የሁለቱም የገንዘብ ድርጅቶች ዋና ተግባሮች በተበዳሪዎች ሃገሮች ላይ ጫና በማድረግ ለሀብታም ባንኮችና ድርጅቶች አራጣን መሰብሰብ ነው።
- እንደ ሩሲያ ኢትዮጵያና ሌሎች ብዙዎች አገሮች ዉስጥ ደግሞ በመንግስት ሥር ተይዘው የነበሩ ኩባንያዎችና የኢኮኖሚ አውታሮች ለግለሰቦች በርካሽ ሲቸረቸሩ እያዩ እንዳላዩ በመምሰል እንዳውም ዝርፊያው በተጣደፈ መልኩ እንዲካሄድ (shock Therapy የሚባለውን አስተሣሠብ በመቀበል) ገፋፍተዋል።
- ታዳጊ አገሮች ከውጭ አገር በሚያስገቧቸው ዕቃዎች (ፍጆታዎች) ላይ የጣሉትን ቀረጥ እንዲያነሡ ሲገፋፉና ሲያስገድዱ፤ በአንፃሩ ግን ሃብታም አገሮች በታዳጊ አገሮች ዕቃዎች ላይ የጫኗቸውን ቀረጦች እንዲያነሡ አላስገደዱም።
- ሃብታም አገሮች ለገበሬዎቻቸው የሚያደርጉት ድጎማ የብዙ ታዳጊ አገሮች ገበሬዎችን ከሥራ ከማፈናቀሉም በላይ (በቅርቡ ኒዮርክ ታይምስ የተባለው ጋዜጣ የሕንድ ገበሬዎችን ጠቅሶ እንደዘገበዉ) ድጎማው ራሣቸውን እስከመግደል አድርሷቸዋል። ይህም በግልጽ እየታወቀ እነዚህ ድርጅቶች ለሃብታም አገሮች መሪዎች ይህንኑ አስቃቂና አሣዛኝ ጉዳይ እንኳ እንዲያቆሙ አንድም ግፊት አላደረጉም።

ከአንዳንድ አሣፋሪ ድርጊቶቻቸውም፦

- ለምሳሌ የጋና መንግስት ከነዚህ ድርጅቶች ብድር ሲጠይቅ ብድሩ እንዲሣካ ከተፈለገ የጋና መንግስት ለተማሪዎች የሚያደርገዉን እርዳታ እንዲቀንስ (እንዲያስወግድ) መጠየቃቸው፤
- የታንዛኒያም መንግስት ብድር ሲጠይቅ በመንግስት ሥር ይተዳደር የነበረዉን የዉሃ ማከፋፈያ ወደ ግል ሃብትነት እንዲያዞር መጠየቃቸውና ለተግባራዊነቱም ማስገደዳቸው፤
- እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1998 ሄሪኬን ሚች (Hurricane Mitch) የተባለው አዉሎ ነፋስ እንደሁንዱራስ ያሉ አገሮችን ሲያጥለቀልቅ እነዚህ አገሮች ከነዚህ ድርጅቶች (በተለይም ከዓለም ባንክ) እርዳታ ሲጠይቁ የቴሌኮሙኒኬሽን መሥሪያ ቤቶቻቸዉን ለግል ባለሃብቶች እንዲሸጡ መጠየቃቸውና ማስገደዳቸው፤
- እንደአእውሮፓውያን አቆጣጠር 2005 ላይ ሱናሚ (Tsunami) ተብሎ የተጠራው የባህር ዉስጥ የመሬት መንቀጥቀጥ እንደሲሪላንካ የመሳሰሉ አገሮችን በዉሃ ሲያጥለቀልቅና አገሮቹ ዕርዳታ ሲጠይቁ በተጎዱት አገሮች ዉስጥ ያሉት ዝቅተና ሰራተኞቸ ሥራቸውን በቀላሉ ሊለቁ እንዲችሉ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ ወይም የደሞዝ ቅነሳን እንዲቀበሉ መንግሥቱ ግፊት እንዲያደርግ (demanding labor flexibility) መጫናቸው ዋነኛ ተጠቃሾች ናቸው።

በዚህም ምክንያት የብዙዎች ምሁራን ተቃውሞ ታዳጊ ሃገሮች በከፍተና ደረጃ ተጎጂዎች መሆናቸውን የሚያመለክት ሆኖ ተገኝቷል። ለጣቂው ጥያቄ ታድያ፦

**ብድሩ ካልጠቀመ ለምን መበደር ያስፈልጋል? ኢትዮጵያስ ለምን በዚህ "ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ" ጉዳይ ውስት ተዘፍቃ ቀረች? የሚል ነው።**

- ያለም ባንክና ያለም የገንዘብ ድርጅት ሃላፊዎች ከሌሎች አገርች ጋር ስናወዳድረው ከኢትዮጵያ ጋር ለየት ያለና የጠበቀ ግንኙነት ወይም ወዳጅነት አለን ይላሉ። አንዳንድ ይህንን የጠበቀ ልዩ ግንኙነት የተከታተሉ ጠበብትና ምሁራን ግን ለዚህ የጠበቀ ግንኙነት ዋና መንስኤው ድርጅቶቹ የሚያወጧቸው የተለያዩና በየጊዜው የሚለዋወጡ (ከብዛታቸው የተነሣም የሚያደናግሩ) መመሪያዎችን ኢትዮጵያ ወደ ኋላ ሳትል ስለምትቀበልና በሥራ ላይ ስለምታውል ነው ይላሉ።
- ጠለቅ ተደርጎ ሲመረመር ግን እነዚህ ድርጅቶች በሚሰጡት ብድር ኢትዮጵያ ተጠቃሚ አትሆንም። ለምን ቢባል እነዚህ ድርጅቶች ያዘዟትን እስከፈጸመች ድረስ ለራስዋ የሚጠቅማትን ማድረግ ስለማትፈቅድና አቅምም ስለሌላት ነው። አቅሟ ስለማይፈቅድላትና እነዚህ ድርጅቶች የሚሏትን አድራጊ ስለሆነችም የአራጣውን አከፋፈል በሚመለከት መከራከር አትችልም።
- አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት የህዝብ ድጋፍ ስለሌለው ደካማ ነው። ስለዚህም የአንዳንድ ሃያላን መንግሥታት ድጋፍን ለማግኘት ሲል ድርጅቶቹ የሚሉትን መቀበል ይገደዳል። ይህ ከሆነም ኢትዮጵያ ከብድሩ ተጠቃሚ ልትሆን አትችልም።
- በኢትዮጵያ ውስጥ ሙሥና (corruption) በጣም ስለተስፋፋ በነዚህ ድርጅቶችም ሆነ በሌላ በኩል የሚሰጠው ብድር በትክክል ሥራ ላይ ስለማይውል ባክኖ ይቀራል፤ ለስርቆሽም ይመቻል። ይህ ጉዳይ ደግሞ በሌሎች ብዙ ድሃ አገሮች ውስጥም የተከሰተ ሃቅ ነው።
- ኢትዮጵያ በብድሩ ተጠቀመች ከተባለም ለምን በየጊዜው ወደ ድህነትና ብድር ትገባለች? የመንግሥትና የህዝብ ሀብት የነበሩት ኩባንያዎችና ተቋሞች ያለአግባብ ለግለሰቦች በርካሽ ሲቸረቸሩ ለምን አበዳሪዎቹ ድርጅቶች ድርጊቱ እንዲቆም አላገዱም ወይም አልመከሩም? እንግሊዝ አገር ውስጥ የሚታተሙ ብዙዎች መጽሄቶች እንደዘገቡት ከአፍሪካ አገሮች ኢትዮጵያንም ጨምሮ (በተለይ ከ1997ቱ የኢትዮጵያ ምርጫ በሁዋላ) ብዙ ገንዘብ ወደ እንግሊዝ ባንኮች መጉረፉ፤ ይህ ገንዘብም ከእንግሊዝ አገር ወደ አፍሪካ ከሚጓዘው ገንዘብ እንደሚበልጥ ተጠቅሷል። እነዚህ ድርጅቶች ገንዘቡን የሚያሸሹትን ግለሰቦች ከየት አመጣችሁት? ብለው ለመጠየቅ ለምን አልተቸገሩም? ብለን ስንጠይቅ ምላሹ አዎንታዊ ለመሆኑ ምስክር አያሻውም።
- በተደጋጋሚ እንደተገለፀውና መረሳት የሌለበት ዋና ጉዳይ የነዚህ ድርጅቶች ዋና የገቢ ምንጮች እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ድሀ አገሮች መሆናቸው ነው። ድሀ አገሮች ብድር ፍለጋ ወደነዚህ ድርጅቶች ሄደው እንዲያጎበድዱ ከተፈለገ ደግሞ በየጊዜው ወደ ተባባሰ ችግር መግባት አለባቸው ማለት ነው! ከላይ እንደተገለጸውም እነዚህ ድርጅቶትች ብድር ካልሰጡ ሊኖሩ አይችሉም! ብድር ካልሰቱም ጨና ማድረግ አይችሉም! ብድር ካልሰጡ እቃ መሸጥ አይገኝም! ብድር ካልተገፋ ለነዚህ ድርጅቶች ለሚሠሩ ሰዎች ሥራ ማጣትንም ያስከትላል! ስለሆነም ድሃ ሃገሮች ከችግር አዙሪት ሳይወጡ ለዘላለም በብድር ተተብትበው ለመኖር መገደዳቸው አይቀሬ ነው፤፡

እነዚህ ሁኔታዎች የሚያሳዩን ቁም ነገር እነዚህ ድርጅቶች ሁኔታው ካልፈቀደላቸው በስተቀር ሁልጊዜም ብድር ለመስጠት ወደኋላ እንደማይሉ ነው! ዎል ስትሪት ጀርናል (*Wall Street Journal*) የተባለው ጋዜጣ ይህ ጉዳይ ሃቅ መሆኑን በተጨባጭ ለማስገንዘብ የዓለም የገንዘብ ድርጅትን (IMF) በሚመለከት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በሚያዚያ 21፣ 2006 ሲዘግብ ከጠቆማቸው ጉዳዮች መካከል፡ 1) የገንዘብ ቀውስ

(financial crisis) ያጋጠማቸው አገሮች ቁጥር ስለቀነሰ 2) አንዳንድ አገሮችም ከዓለም የገንዘብ ድርጅት የሚያገኙትን ብድር ትተው ከሌሎች አገሮች መበደርን ስለመርጡ፤ ድርጅቱ (IMF) ወደ 600 ሚሊዮን የአሜርካን ዶላር ያህል ክስረት እንደደረሰበትና፤ ሠራተኞቹን ለማቆየት ሲል ባራጣ ወዳከበተው የወርቅ ሃብቱ እጁን ለመክተት እንደተገደደ፤ በተለይም በተበዳሪዎች ላይ ያደርግ የነበረው ጫና እና ግፊት ስለተቀነሰበት መቆጨቱንና አንዳንድ አገሮችም (ለምሣሌ ደቡብ ኮሪያና አርጀንቲና) ድርጅቱ የገጠመዉን ጉዳይ ጠቅሰው ደስታቸውን በይፋ "እሠየው፤ ለኛ የደረሰብን ችግር በከፊሉም ቢሆን እንኳን ይህ ድርጅት ቀመሰው" ብለው እስከመናገር ደርሰዋል። ኢትዮጵያን በተመለከተም፦

- የኢትዮጵያ ህዝብ የምርጫው ዉጤት ባሸባሪው የሕወሃት አገዛዝ ተሠርቆበት ባለበት ሁኔታ ለዚሁ አሸባሪ አገዛዝ በሚያደርጉት ጭፍን ድጋፍ ሲቆጣ ብድሩን አንሠጥም ካሉ በኋላ ተመልሰው ግን ቃላቸውን አጥፈው እርዳታውን ቢያግተለትሉት ሊገርመን አይገባም! ከምርጫው በኋላ የመለስ ዜናዊ መንግስት ከሥልጣን ሊወርድ ይችላል የሚል ጥርጣሬ ስለነበራቸው ከተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር (ምናልባት ሥልጣን ከያዙ በሚል ግምት) ለማበር ፈልገው ነበር። ውሎ ሳያድር አባባላቸው ባንድ ራስ ሁለት ምላስ ሆነ። አቸናፊ ሆኖ የሚወጣው ሀይል ሥላልታወቀ ነበር ያመነቱት። መረሳት የለለበት ነገር ቢኖር እነዚህ ድርጅቶች ሁልጊዜም ካቸናፊ ሃይል ጋር (ለጊዜዉም ቢሆን) መሆንን ይመርጣሉ!
- በውጭ ሃይሎች ትብብርና እገዛ ጭምር የተቃዋሚዉ ሀይል እየተፍረከረከ ሲመጣ፤ በሥልጣን ላይ ያለዉም መንግስት የበላይነቱን ለጊዜዉም ቢሆን ሲያረጋግጥ፤ የመለስ መንግስት ስለሚታዘዛቸውና በዚህም ባህርይው ስለሚወዱት ብድሩን አግተለተሉት!

ስለዚህም እትዮጵያዊያን መገንዘብ የሚገባቸው እነዚህ ድርጅቶች ምን ጊዜም ቢሆን የሃያላን አገሮችን ጥቅም አስጠባቂ መሆናቸውን፤ የሃያላን አገሮችን ትእዛዝ አስፈጻሚ መሆናቸውን፤ ሁልጊዜም በብድር ስም ገፈፊዎች መሆናቸውንና ብድር ካልሰጡ ሊኖሩ የማይችሉ መሆናቸውን ነው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቃዋሚ ሀይሎች በጋራ ሥልጣን ካሸባሪው መንግስት ካስለቀቁ እነዚህ ድርጅቶች የአቸናፊውን ሃይል እንደሚደግፉ ማወቅ ተገቢ ነው። ከነዚህ ድርጅቶች በየጊዜው የሚጎርፈው ገንዘብ "እርዳታ" ተብሎ ቢጠራም እርዳታ ሣይሆን ብድር መሆኑንም መዘንጋት አይገባም!

አንዳንድ ጊዜም እርዳታ ተብሎ ወደ አገራችን የሚገባው እህል እንኳ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል! እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በድርቅ የተነሣ ህዝቦቿ ርሐብ ከሚያጠቃት፤ ርዳታም ከሚሠጣት አገሮች አንዷ ናት። ድርቅ ኢትዮጵያን አጠቃት ሲባል ሁሉም ቦታ ወይም ክፍለ ሀገር ድርቁ ገባ ማለት አይደለም። እንዳዉም አንዳንድ ቦታዎች (ክፍለ ሃገሮች) ድርቅ ሊያጠቃቸው ቀርቶ ምርት ይትረፈረፍባቸዋል። ይህ በመሆኑም አንዳንድ ያገሪቱን ቦታዎች ድርቅ ሲያጠቃቸው መደረግ ያለበት ምርት ከተርፋቸው ኢትዮጵያዉያን እህሉ ተገዝቶ ድርቁ ለጎዳቸው ቦታዎችና ስዎች ማደል ነው። ጉዳዩን የተከታተሉ ብዙ አዋቂዎችና የኤኮኖሚ ጠበብቶች በጥናት እንዳረጋገጡት ይህን ማድረግ ከተቻለ ጥቅሙ ብዙ ነው።

1. ያገሪቱ (የኢትዮጵያ) ገበሬዎች በየጊዜው ብዙ ምርት እንዲያመርቱ ያበረታታል፤
2. ከውጭ አገር "በነፃ ዋጋ" የሚገባው እህል ባገሪቱ ውስጥ የሚመርተው እህል ዋጋው እንዳይረክስ ያደርጋል፤
3. እርዳታው በሚላክበት አገሮች የሚኖሩት ገበሬዎች በመንግሥታቸው ድጎማ የተነሣ ብዙ ምርት እንዳያመርቱና በአለም ላይ የሚመረተውን የእህል ዋጋ እንዳያወርዱ

ያደርጋል።

4. ለእርዳታው እህል ማጓጓዣ የሚጠፋውን ገንዘብ ይቀንሳል፤ ለቁጠባም ያግዛል። ለምሣሌ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ጥቅምት 26 2005 ዎል ስትሪት ጆርናል የተባለው ጋዜጣ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ሲዘግብ፤ የአሜሪካ መንግስት የእርዳታውን እህል ከአሜሪካ አስጭኖ በመላክ ፈንታ ከኢትዮጵያ ገበሬዎች እህሉን ቢገዛና ለተራቡት ወገኖቻችን ቢያድል ብዙ ገንዘብ እንደሚያተርፍና በተለይም ሀምሣ ሽህ ያሕል የሰው ህይወት ማዳን እንደሚቻል አስገንዝቦ፤ ነገር ግን ይህ እንዳይሆን እህሉን ለአሜሪካ መንግስት የሚሸጡት ሀብታም ገበሬዎችና እርዳታውን የሚያድሉት የቤተ ክርስቲያን ተወካዮች አሻፈረኝ በማለታቸው እርዳታው በድሮው መልኩ እንዲቀጥል ሆኗል! ጉዳዩን ተግባራዊ ያደረጉት የፕሬዚደንት ቡሽ ተወካይ ሚስተር አንድሩው ናሲዎስ ላይም ከፉኛ ውርጅብኝ ደርሶባቸዋል! ይህን ጉዳይ የተከታተሉት ታዛቢዎች ደግሞ “ለመሆኑ እርዳታውን የሚያድሉት ቤተክርስቲያኖችና ተወካዮቻቸው በእውነት የቆሙት ለአሜሪካ ሀብታም ገበሬዎች ነው ወይስ እርዳታውን ለሚቀበሉት ተራቢወች አገሮች?” ብለው እንዲጠይቁም አስገድዷቸዋል።

የአበዳሪ ድርጅቶች መሪዎችም ቢሆኑ የተሾሙ አለቆች እንጂ ለህዝብ አሣቢና ተቆርቋሪ ካለመሆናቸውም በላይ፤ የታዳጊ አገሮችን ችግሮች የማያውቁ፤ ሙያቸው የኢኮኖሚ ጠበብትነት ያልሆነ፤ የአንዳንድ ሃያላን አገሮች መሪዎችን ደጋፊ ብቻ የሆኑ፤ አንዳንዶቹም በአቋማቸው የቀኝ መስመር አክራሪዎችና ደጋፊዎች (ለምሣሌ እንደነ ዎልፎዊዝ ያሉት) ናቸው። ገመናቸውን ለመሸፈንና ያልሆኑትን ነን ለማለትም አንዳንድ እርምጃዎችን ከመውሰድ ጭምር አይታቀቡም። በቅርቡ ከሥልጣናቸው እንዲወርዱ የተገደዱት ሚስተር ዎልፎዊዝ ገና ስልጣን እንደተረከቡ ሥራቸውን የጀመሩት በቀጥታ ወደ አፍሪካ በመገስገስ ነው። ከአፍሪካ ከጎበኟቸው አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ሥትሆን ሌላዋ ሴኔጋል ነች።

ሚስተር ዎልፎዊዝ እነዚህን አገሮች ለመጎብኘት ከመረጡበት ምክንያቶች መካከል፦

1. አገሮቹ በጣም ድሃ ሥለሆኑ ድሃ አገሮችን ሲጎበኙ ልባቸው ስለሚረካና ከድሃ ሠዎች ጋር ፎቶ ሲነሡ ለድሃ አሣቢና ተቆርቋሪ ስለሚያስመሥላቸው፤
2. የነዚህ አገር መሪዎች፤ በተለይም የኢትዮጵያው መሪ የድርጅታቸውን መመሪያዎች አሜን ብሎ ሥለሚቀበልና ይቀበልም ሥለነበር እንጂ ለድሃ አገሮችና ህዝቦች አስበው አልነበረም።

እውን ለድሃ አገሮች የሚጨነቁ ቢሆን ኖሮ ሚስተር ዎልፎዊዝ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ሙሥናን (corruption) እጠላለሁና (ላገርዎም ስለማይበጅ) እባከዎ አቶ ዜናዊ ሙሥናን ካገረዎ ያስወግዱ ብለው ሊጠይቁ ይገባቸው ነበር። ይህንን ጨርሶ አላደረጉም። ዓላማቸው አይደለምና።

**ስለአበዳሪ ድርጅቶች የበለጠ ማወቅ ከፈለጉ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ማሥረጃዎች ያንብቡ።**

References (easily readable, non-technical!)

Easterly, William R., "Africa's Poerverty Trap" *The Wall Street Journal*, March 23, 2007, p. A11.

Moffett, Matt and Bob Davis, "Insufficient Fund: Booming Economy Leaves the IMF Groping for Missio," The Wall Street Journal, April 21, 2006, Beginning on page A1.

Rodrik, Dani, "Goodbye Washington Concesnsus, hello Washington Confusion? A review of the World Bank's Economic Growth in the 1990s: Learning from a Decade of Reform." *Journal of Economic Literature*, Volume XLIV (December 2006), pp. 973-87.

Klien, Naomi, "Sacrificial Wolfie." CommonDreamsorg NewsCenter, Monday, April 30, 2007.

King JR, Neil and Gregg Hitt "Mission Adjustment: Key Issue for the World Bank: How to Tackle Corruption." *The Wall Streent Journal*, May 14, 2007, beginning g on page A1.

Thurow, Roger and Scott Kiman, "Farmers, Charities Join Forces to Block Famine-Relief Revamp." *The Wal Street Journal*, October 26, 2005, beginning on page A1.

Kilman, Scott and Roger Thurow, "Pork Chops: In Fight Against Farm Subsidie, Even Farmers Are Joining Foes: A Snowballing Movement Draws Churches, CEOs; Huge Hurdles in Congress." *The Wal Street Journal*, March 14, 2006, beginning on page A1.

Sengupta, Somini, "On India's Farms, a Plague of Suicide." *The New York Times*, September 19, 2006.

*Gemeda Humnasa:* "Corruption issues in Ethiopia's southern State," *American Chronicle,* December 19, 2006, available at:

http://www.americanchronicle.com/articles/viewArticle.asp?articleID=18149.

*Combating corruption in Ethiopia, Tuesday August 17, 2004*
*Available at*
*http://www.capitalethiopia.com/archive/2004/august/week3/bussiness%20and%20law.htm#top*

Prime Minister gets rid of Auditor who exposed government's corruption,
Available at: http://ethiopianpolitics.blogspot.com/2006/11/prime-minister-meles-gets-rid-of.html